# *በአዲስ ዓመት በጎ ምኞት*

በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ የሚመላለሱ ምኞትና ፍላጎቶች ዓይነታቸው ብዙ ሲሆን፣ እነዚህን በአጠቃላይ፤

ሀ) የሚደረስባቸውና የማይደረስባቸው
ለ) ክፉና በጎ ምኞቶት በሚል አገላለጽ በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል።

የሚደረስባቸው ምኞቶች ሰው በሕይዎት ዘመኑ ሊያከናውን የሚያስባቸው ራዕዮች (ግቦች) ሲሆኑ እነዚህ የሕይወት አቅጣጫ ጠቋሚ ወይም የተስፋ ስንቅ በመሆን ግለሰቡ ለሥራ እንዲነሳሳ ይረዱታል። የማይደረስባቸው ምኞቶች ግን የግለሰቡን አእምሮ በመበዝበዝና በማዳከም ተስፋ ቆራጭ፣ ለሥራ የማይነሳሳ ሰነፍ እንዲሆን ያደርጉታል። በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጡት ክፉ ምኞቶች በቤተ ክርስቲያን ቋንቋ የሥጋ ፍሬዎች ተብለው የሚታወቁ ሲሆኑ፣ እነዚህ ሥጋዊ ፍላጐቶች ግለሰቡ ተሳክቶለት ቢፈጽማቸው በወንጀለኛነት የሚያስጠይቁ፣ ባይደረስባቸውና በምኞት ብቻ በሰው አእምሮ ውስጥ ተሰንቀው ቢቀሩም በኃጢአትነት የሚመዘገቡ ናቸው።

በአጠቃላይ የሰው ልጅ ምኞትና ፍላጎት የተለያየ የመሆኑን ያህል በአንጻሩ ደግሞ የአንድ አገር ሕዝቦችንና የአንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆችን አንድ የሚያደርጉ (የጋራ የሆኑ) ተመሳሳይ ፍላጎቶች ይኖራሉ። ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ ኦርቶዶክሳዊያን እንደ ክርስቲያን ሁላችንንም አንድ የሚያደርጉ የጋራ ምኞትና ፍላጎቶች አሉን። ከእነዚህም፤

ሀ) የሀገር ብልጽግና
ለ) የቤተ ክርስቲያን ሰላምና
ሐ) የሕዝብ አንድነት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እነዚህ ሦስት ነገሮች በሐሳብ ደረጃ ተነጣጥለው ይቀመጡ እንጅ በአፈጻጸም ተወራራሽና ተደጋጋፊ ናቸው። በአንድ አገር ሕዝቦች መካከል አስተማማኝ አንድነት ካለ ሰላም አለ። ሰላም ካለ ደግሞ ሠርቶ ለማደግ ያለው እድል ሰፊ በመሆኑ ከሀገር እየወጣ የሚፈልሰው የተማረ የሰው ኃይል ቁጥር ይቀንሳል። መቸውንም ቢሆን ቸግሮት ካልሆን በስተቀር ነጻነቱን አጥቶ በስደት መኖርን የሚመርጥ ዜጋ የለም። በስደት ዓለም ስንኖር በዕለት ተዕለት የኑሮ ገንኙነታችን እንደሚደመጠው ለሀገሩ እድገትና ሰላም የሚጨነቀውና፣ ሠርቸ ገንዘብ አገኝቸ ወደ ትውልድ ሀገሬ እመለሳለሁ የሚለው ኢትዮጵያዊ ቁጥሩ ቀላል አይደለም።

እንግዲህ ለመንደርደሪያ ያህል ሁላችንንም አንድ የሚያደርግ የጋራ ምኞታችንና ፍላጎታችን ምን እንደሆነ ከተረዳን በልባችን የተንጠለጠለው ጽኑ ምኞታችን እንዳይሳካ መሰናክል የሆኑብንን ነገሮችን ለይተን በማመልከት የእኛ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚገባ ቀጥለን እንግራለን።

### *ምኞታችን እንዳይሳካ እንቅፋት የሆነብን፣ ሰላምና አንድነታችንን የወሰድብን ማን ነው?*

ዛሬም ነገም ልጆቹ ነንና “ሰላሜን እሰጣችኋለሁ” (ዮሐ 14:27) ብሎ የተናገረ የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንዳላጠፋብን እምነታችን የጸና ነው። እንግዲያውስ ለሰላማችን መደፍረስና ለአንድነታችን መናጋት ምክንያቶች ምንድር ናቸው ተብለን በዚህ ዘመን ያለን ኢትዮጵያውያን ብንጠየቅ ሁላችንም ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የተለያዩ ነገሮችን መዘርዘራችን አይቀርም። በተጨባጭ ሲታይ ግን ዋና ዋና መሠረታዊ ነጥቦቹ ሁለት ብቻ ናቸው። እነዚህም በጳጳሱ ወይም በሀገር መሪው፣ በቄሱና በመነኩሴው፣ በወንጌል ሰባኪውና በዘማሪው <u>በሁላችንም</u> አእምሮ ውስጥ ተደብቀው የሚኖሩ <u>የጎሰኝነትና የራስ ወዳድነት</u> በሽታዎች ናቸው። ጎሰኝነት (ትራይባሊዝም) እና ራስ ወዳድነት (ኢጎይዝም) በባሕርያቸው ተወራራሽ ሲሆኑ ከጠባብ አስተሳሰብ (ሴክቴሪያን ማይንድሴት) የሚመጩ ናቸው። የጎሰኝነት በሽታ የተጠናወተው ሰው ከአካባቢው ሰው ውጭ ሌላውን አያምንም። የዘውትር ጸሎቱም ጠላቶቸ በሚላቸው ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ርግማን ነው። የራስ ወዳድነት በሽታ ያጠቃው ሰው ደግሞ ምኞቱና ሕልሙ በገንዝብና በቁሳቁስ ከሰው ልቆ መታየት ስለሆነ ለጥቅም ሲል ራሱንና የሃማኖቱን ክብር ያዋርዳል። ወዳጅነቱም ጥቅሙን ከሚያስከብሩለት ጋራ ብቻ ይሆናል። ማንም ኢትዮጵያዊ ስለ ጎሰኝነት ቢጠየቅ “እኔ ብሔራዊ ስሜት ነው ያለኝ” የሚል መልስ እንደሚሰጥ ጥርጥር የለውም። በተግባር ግን ከራስ ወዳድነትና ከጎሰኝነት የጸዳ ሰው እንደሌለ በፖለቲካው መስመርና በሥራ ዓለም የሚስተዋለውን ሳይጨምር በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም በየቤተ ክርስቲያኑ የሚሰማው መላቀስና መካሰስ ትክክለኛ ማስረጃ ነው። በተለይም ደግሞ መንጋውን አንድ አድርገው

እንዲመሩ መለኮታዊ አደራ የተጣለባቸው የሃይማኖት አባቶች የዘር ኃረግ እየቆጠሩ ለሚያገለግሉት መንጋ የመለያየት ምሳሌ እየሆኑ መምጣታቸው የችግሩን ስፋት የሚያመለክት ነው።

በአሁኑ ጊዜ በስደት ዓለም በምትኖር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያለን ካህናትና ምዕመናን በየዕለቱ የሚያስጨንቀን በቤተ ክርስቲያን ሰላም ጠፋ፤ አንድነታችን ተናጋ፣ ለቀጣዩ ትውልድ የምናስተላልፈው ታሪካዊ ውርስ አጣን? የሚለው በጎ ሐሳብ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው የማባረርና የመባረር ፍልሚያ እኔ አሸናፊ ሳልሆን ቀረሁ የሚለው እልህ ነው። በአጠቃላይ የሃይማኖት መሪው በመንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ ከምዕመን አንሶ የሚስተዋልበት፣ ካህን ካህንን እንደ ጦር የሚፈራበት፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ከልባችን ተፍቆ እየተራገምን የምንቀድስበት፣ እውነት በሰው አንደበት የማይነገርበት፣ መተማመን የጠፋበት ዘመን ቢኖን ይህ ዘመን ነው። በእንደዚህ ዓይነት አስቸጋሪ ሕይወት አልፈው ቤተ ክርስቲያንን ለመረከብ የተዘጋጁ ንጹሕ ዜጎች ይሆናሉ ብሎ ከልጆቻችን በጎ ነገርን መጠበቅ ስንፍና ነው።

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ እየተባባሰ ለመጣው የቤተ ክርስቲያን ሰላምና የሕዝብ አንድነት መናጋት በተናጠል ብቸኛ ተጠያቂ የሆነ ግለሰብ ወይም ቡድን እንዳለ አምኖ ራስን ከተጠያቂነት ነጻ ለማድረግ መሞከር "ዓይንህን ጨፍንና ላጃጅልህ" እንደማለት ነው። ይልቁንስ ሁላችንም ለችግሩ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ እንዳደረግን አምነንና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የመፍትሔ ሐሳቦች ተቀብለን ለመፍትሔው ራሳችንን ብናዘጋጅ የተሻለ አማራጭ ይሆናል።

## *ሀ) ራስን መመርመርና ለቤተ ክርስቲያን ሳላምና ለሕዝብ አንድነት ሲባል አስተሳሰብን መለወጥ፣*

አገሬንና ቤተ ክርስቲያኔን እወዳለሁ፣ የሕዝቤንም አንድነትና ሰላም አጥብቄ እመኛለሁ የሚል ዜጋ በቅድሚያ የራሱን ፍላጎት በሕዝብ ፍላጎት ለውጦ፣ ወገንተኛ አስተሳሰብንና ራስ ወዳድነትን ከአእምሮው ፍቆ ራሱን የሰላም ሐዋርያ አድርጎ ማዘጋጀት አለበት። በውስጣችን የተዳፈነውን የልዩነት መንፈስ ሳናስወግድ፣ ሳንለወጥና ራሳችንን ለአንድነት ሳናዘጋጅ ሰላምና አንድነትን ብንመኝ ወይም የራሳችንን ችግር በሌላው በማሳበብ ችግሮችን ሸፋፍነን ለማለፍ ብንሞክር ከመቋሰልና ከመላቀስ ነጻ እንሆንም። የጌታ ቃል እንዲህ ይላል፣ "ሰላም ሳይሆን፣ ሰላም ሰላም ይላሉ። ሰላምን በተስፋ ተጠባበቅን፥ መልካምም አልተገኘም መጠገንን በተስፋ ተጠባበቅን፥ እነሆም፥ ድንጋጤ ሆነ። ምላሳቸው የተሳለ ፍላጻ ነው፤ ሽንገላን ይናገራሉ፤ ሰው ከባልንጀራው ጋር በሰላም ይናገራል፥ በልቡ ግን ያደባበታል" (ኢሳ 8፡11)።

እግዚአብሔርን አምናለሁ ስለ እውነት እቆማለሁ የሚል ክርስቲያን ወንድሙን ሲያጠቃ በደስታ የሚቧርቅ፣ ሲሸነፍ እንደ ሕጻን የሚያለቅስ፣ በሌላው ላይ ጣቱን አዘውትሮ የሚቀስር፣ አንተ ጥፋተኛ ነህና ይቅርታ ጠይቅ ሲባል ተደፈርኩ ብሎ ፊቱን አዙሩ የሚሸሽ ሊሆን አይገባምና ክርስትናችን በኑሮ ይገለጽ።

## *ለ) የሌሎችን በጎ አርአያነት መከተል፣*

በምንኖርበት በአሜሪካን ሀገር ከእኛ ከሐበሻ በትውልድ ሐረግ፣ በቆዳ፣ በዓይንና በጸጉር ቀለም የሚለዩ አሜሪካውያን ከየትኛውም ሀገር እየፈለሰ የሚመጣውን ስደተኛ ሁሉ በእኩልነት በማክበር "በአገራችሁ ውስጥ ከእናንተ ጋር እንግዳ ቢቀመጥ ግፍ አታድርጉበት። እናንተ በግብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና ከእናንተ ጋር የሚቀመጥ እንግዳ እንደ አገር ልጅ ይሁንላችሁ፥ እርሱንም እንደ ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ" (ዘሌ 19:33) የሚለውን የፈጣሪ ቃል በተግባር ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ። በተቃራኒው ግን ትክክለኛውን የኦርቶዶክስ እምነት እንከተላለን የምንል፣ ተመሳሳይ የዘር ሐረግ፣ ተመሳሳይ መለከና ቀለም ያለን እኛ ሐብሾች ይህን አምላካዊ ቃል በተግባር በሥራ መተርጎም ተስኖን አእምሯችን በፈጠረው "የእኛነት" ስሜትና በመንደርተኝነት ጣጣ አንድነታችን ፈተና ላይ እንዲወድቅ አድርገናል። ከዚህ ቀደም በተላለፉ ጽሑፎች ጉሰኝነት በሽታ ነው ለማለት የደፈርኩት "የእስራኤል ልጆች ሆይ፥ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? " (አሞ 9:7) በማለት ቸሩ አምላክ እኛን ጥቁሮችን በቆዳ ቀለማቸውና በዘር ሐረጋቸው ከሚመኩ ከእስራኤል ጋር እኩል አድርጎን ሳለ አንዱ ሐበሻ ከሌላው የሚበልጥበት ምንም ዓይነት መሠረታዊ ምክንያት ሳይኖር እርስ በራሳችን መለያየታችን እሳፋሪ በመሆኑ ነው።

## *ሐ) ለሃይማኖት ሕጎች ተገዥ መሆን፣*

መድኃኒታችን ክርስቶስ የተወለደው በእምነታቸውና በዘር ኃረጋቸው ከሚመኩ አይሁድንና በጣኦት አምልኮ ከሚታወቁ አሕዛብ ከሁለቱም የትውልድ ኃረግ ነው። ዓላማውም የሰው ልጆችን እኩልነት ማረጋገጥና በዘር ኃረግና በአመለካከት

የተለያዩትን በአንድ የእምነት ጥላ ስር ማሰባሰብ ነው። ይህን በቃሉ ደጋግሞ አስተምሯል። ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ሲመሰክር፣ “አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና” (ገላት 3:28) ብሏል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንና አንድነት የሚታወጅባት፣ አገልጋዮቿ ካህናት ከጠባብ አስተሳሰብ የሚመነጩ ልዩነቶችን የሚቃወሙ የክርስቶስ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይገባል።

ሰው የተፈጥሮ አካሉን በስለት ቆርጦ ቢጥል የሚታዘንለት ራሱን መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን የፈጣሪን ሕግ በመተላለፉ ሌላ ተጨማሪ ፍርድ የሚጠብቀው በመሆኑ ጭምር ነው። የታመመው አንድነታችን እንዲፈውስ የቤተ ክርስቲያን ሰላም እንዲመለስና ተሸማቀው በየቤታቸው የተቀመጡ ወገኖቻችን በፍቅር ከእኛ ጋራ ለአምልኮት እንዲቆሙ “በእኔነት” ስሜት ወንድሙን ያሳዘነ ሁሉ ይቅርታ እንዲጠይቅና ንስሐ በመግባት ራሱን ከመለኮታዊ ፍርድ ነጻ እንዲያደርግ ያስፈልጋል። “ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው። እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና” (ሮሜ 2:9) ተብሎ እንደተጻፈ። ምክንያቱም የሕዝብ አንድነትና የቤተ ክርስቲያን ሰላም በይቅርታ፣ በመቻቻልና በመከባበር ነው እንጅ በመፎካከር የሚመጣ አይደለምና።

ስለዚህ በአዲሱ ዓመት በአእምሯችን ተሰንቆ የኖረውን አሮጌ አስተሳሰብ በንስሐ እንደ እባብ ለብስ አውልቀን ጥለን፣ አዲሱ ትውልድ የሚፈልገውን የፍቅርና የመቻቻልን መርህ ልንከተል ያስፈልጋል። ፍቅር ሰላምንና አድነትን፣ አንድነት ደግሞ እድገትን ይወልዳልና።

የልዑል እግዚአብሔር ቸርነት፣ የቅድስት ድንግል ማርያም ምልጃና በረከት፣ የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለየን፤ አሜን።

ቀሲስ ዘመነ ደስታ
ሳን ሆዜ
ካሊፎርንያ